# የአረንጓዴ ልማት ከየት ወዴት?

በአብዱልአዚዝ ዩሱፍ

09-03-14

- ❖ የተለጠጠው የአረንጓዴ ልማት ዕቀድ

- ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ጋር ያለው ቁርኝት
- የአረንጓዴው ዕድገት አማራጭና፣ አዋጭነት
- ለአለም አቀፉ ማህበረሰብና ለአከባቢው ሀገራት ያለው ፋይዳ
- ተግዳሮት

ኢትዮጵያ በአለማችን ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ ከሆኑ 10 ሀገራት መካካል አንዷ መሆኗን የመንግስታቱ ድርጅት የአከባቢ ጥበቃ ድርጅት (UNEP) ጥናት ያመለክታል፡፡ በአማካይ ሙቀት መጠን መጨመርና የዝናብ ስርጭት መዛባት የመሰሉ ቀጥተኛ የሆኑ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎች ተጠቂ ናት፡፡ የአገሪቱ 80 በመቶ ዜጎች መተዳደሪያ እንዲሁም 40 በመቶ ሀገራዊ ምርት የተመሰረተበት የግብርናው ዘርፍ፣ የአየር ንብረት ለውጡ ቀጥተኛ ተጠቂ መሆናቸው ተጋለጭነቱን ያባብሰዋል፡፡

የአየር ንብረት በአለማችን ላይ ከደቀነው ተጨባጭ አደጋ ባሻገር የዘላቂ ልማት አማራጮችን ይዞ መምጣቱ አልቀረም፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ከፍተኛ አደጋ ተቋቋሞ እስከ 2017 መካከለኛ ገቢ ያላትን አገር ለመፍጠር ካለው ብርቱ ፍላጎት የተነሳ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂን ቀርጿል፡፡

በቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መሪነት በየካቲት ወር 2003 ዓ.ም የተቀረጸው የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ፣ ኢትዮጵያ ያቀደችውን የተለጠጠ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማሳካትና የሙቀት አማቂ ጋዞችን መቀነስ የሚያስችሉ አማራጮችና ዕድሎችን መለየት ዋናው አለማው ነበር፡፡ መንግስት በዘርፉ የተሻለ ልምድ ያላቸውን የልማት አጋር አካላትን ለመሳብ ጥረት እንደሚደረግም ስትራቴጂው ያመለክታል፡፡

ኢትዮጵያ በተለመደው የኢኮኖሚ ዕድገት አማራጭ ብትጓዝ በ2002 ዓ.ም የነበራት 150 ሚልዮን ቶን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት በ2022 ዓ.ም ከዕጥፍ በላይ በማደግ 400 ሚልዮን ቶን ይደርሳል፡፡

የልማቱ አማራጩ አብዛኛውን የአገሪቱን ጠቅላላ ምርት ነዳጅና ተመሳሳይ የሀይል ምንጮችን ከውጭ በማስገባት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሀገሪቱን ለውጭ ምንዛሪ ዕጥረት ይዳርጋታል፡፡ ለአብነትም በአምስቱ የልማትና ትራንስፎርሜሽን አመታት ከሚያስፈልገው 50 ቢልዮን የአሜሪካ ዶላር ገሚሱ ገንዘብ የሚያስፈልገው በውጭ ምንዛሪ መልክ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የምትከተለው የአረንጓዴ ልማት ዕድገት አማራጭ ምንነት፣ ከልማትና ትራንስፎርማሽን ዕቅዱ ጋር ያለው ቁርኝት፣ አዋጭነት፣ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብና ለአከባቢያዊ ሀገራት ያለው ፋይዳ እንዲሁም ተግዳሮቱን ለመዳሰስ ተሞክራል፡፡

## የተለጠጠው የአረንጓዴ ልማት ዕቀድ

የአየር ንብረት ለውጥ ታሪካዊ ሀላፊነት ያለባቸው የበለጸጉት ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ የሚያመጣውን ተጽኖ ለመቀነስ የታዳጊ አገራት ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ተገንዘበዋል፡፡ ከተለያዩ እንዱስትሪዎች የሚመነጩትን ሙቀት አማቂ ጋዞች መጠን ከመቀነስ (Mitigation) አንስቶ ከችግሩ ጋር ለመላመድ (Adabtation) የአለም ሙቀት መጠን ከእንዱስትሪው አብዮት በፊት ከነበረው የሙቀት መጠን ከ1 ነጥብ 5 ዲ.ሴ በላይ እንዳይጨምር የአለም መሪዎች በኳታር በተካሄደው የዶሃ ጉባኤ ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ ታዳጊ ሀገራት አረንጓዴ ልማት ዕቅድን ለመተግበር ለሚያከነውኗቸው ተግባራት ከቴክኖሎጂ ድጋፍ አንስቶ እስከ ፋይናንስ ድጋፍ ማድረግም የስምምነቱ አካል ነው፡፡

ከታዳሽ ሀይል በተለይም ከውሃ ሀይልን በማመንጨት በተነጻጻሪ ከሌሎች ሀገራት ቀድማ አረንጓዴ ልማትን መተግበር የጀመረችው ኢትዮጵያ፣ ሀገሪቱ ለአየር ንብረት ለውጥ ያላትን ተጋላጭነት በፍጥነት የአረንጓዴ ልማት ማስፈጸሚያ ስትራቴጂ ቀርጻለች፡፡

የግብርናውን ዘርፍ ማዘመን፣ የደን ልማት፣ ታዳሽ ሀይል አማራጭ መከተል እንዲሁም የትራንስፖርት፣ የኢንዱስትሪ የቤት ልማትን በተስማሚ ቴክኖሎጂ መተግበር የአገሪቱ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂው መሰረቶች ናቸው፡፡ የስትራቴጂው መሰረቶች አተገባበር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያው የስትራቴጂው መሰረት የግብርናውን ዘርፍ ማዘመን ነው፡፡ ዘርፉ የአገሪቱ ኢኮኖሚ መሪ ዘርፍ መሆኑና የአብዛኛው የሀገሪቱ ዜጎች መተዳደሪያ መሆኑ ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ አድርጎታል፡፡ የግብረናውን ዘርፍ ለማሳደግ ከዚህ ቀደም በተለምዶ እንደሚደረገው የሚታረስ መሬትን ማስፋፋትና የቀንድ ከብቶችን ቁጥር ከማሳደግ ይልቅ የመሬትንና የቀንድ ከብቶችን ምርታማነት ማሳደግ የአረንጓዴ ልማት አቅጣጫ ነው፡፡

የተሻሻሉ የሰብልና የቀንድ ከብት ዝርያዎችን አርሶ አደሩ እንዲጠቀም ማድረግ የግብርና ዘርፍ ማሳደጊያ ሰልት ነው፡፡ የደን ጭፍጨፋን ለመቀነስ በተለይም በተራቆቱና በተጎዱ አከባቢዎች ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እንዲሁም ከፍተኛ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋትም በስትራቴጂው የተያዘ ዕቅድ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂው የተመሰረተው የደን ሃብት ልማት ላይ ነው፡፡ በኢትዮጵያ፤ ደን 80 በመቶ ለሚሆኑ በተለይም በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል ለሚኖሩ ዜጎች የሀይል ምንጭ ነው፡፡ ከዚህ ንብ በማነብ፤ የጫካ ቡና እና ከጣውላ የሚገኘው ምርት የጠቅላላ ሀገራዊ ምርትን 4 በመቶ ድርሻ ይዛል፡፡ በተለይም የአፈርና ውሃ ጥበቃ፣ ብዝሃ ህይወትን ለመጠበቅ እንዲሁም ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሆኑትን ሙቀት አማቂ ጋዞችን በማምከን ረገድ የደን ዘርፉ የማይተካ ሚና አለው፡፡ የተለመደው የኢኮኖሚ ዕድገት አማራጭ ከቀጠለ እስከ 2022 ዓ.ም ባለው ጊዜ 9 ሚልዮን ሄክታር ደን ይመነጠራል፡፡

ለአገሪቱ ጤናማ ዕድገት ከፍተኛ ሚና ያለው የደኑ ዘርፍ ጉዳት ለመቀነስ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ስልቶችን ቀይሷል፡፡ ዜጎች ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን እንዲጠቀሙ

ማድረግ፤ ከማገዶ ውጭ ( በኤሌክትሪክ፣ ባዮጋዝና በተፈጥሮ ጋዝ) የሚሰሩ ሚድጃዎች ህብረተሰቡ እንዲጠቀም በማድረግ የደን ምንጠራን ትርጉም ባለው መጠን መከላከል የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂው ሌላው ስልት ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለ ጎን የተጎዱ መሬቶችን በመከለል እንዲያገግሙ ማድረግና ተጨማሪ መሬትን በደን በመሸፈን የደን ልማቱ እንዲስፋፋ የሚያደርጉ ስልቶች ናቸው፡፡

ለአገር ውስጥና ለአከባቢያዊ ፍጆታ የሚያስፈልገውን የኤሌክትሪክ ሀይል ፍጆታን፤ ከታዳሽ የሀይል ምንጮች ማስፋፋት የስትራቴጂው ሶስተኛ መሰረት ነው፡፡ ኤሌክትሪክ ለዘመናዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ የሀይል ምንጭ ነው፡፡ ከከተሞችና እንዱስትሪዎች የሀይል ፍጆታ አንስቶ ለመስኖ የሚያስፈልገውን ውሃ ለመግፋት ይዉላል፡፡ በአማካይ ከ10 በመቶ በላይ የሚያድገው የሀገሪቱ አኮኖሚ በአመት ከ14 በመቶ በላይ የኤሌክትሪክ ሀይል ያስፈልጓል፡፡

ኢትዮጵያ ከራሷ አልፎ ለሎች የሚተርፍ ዕምቅ ታዳሽ ሀይል አማራጭ እንዳላት በዘርፉ የተሰሩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

ኢትዮጵያ ከታዳሽ የሀይል ምንጮች ብቻ 60 ሺህ ሜጋ ዋት ማመንጨት የሚያስችል ዕምቅ አቅም አላት፡፡ ከዚህም ውስጥ የሀይድሮ ዘርፉ 45 ሺህ ሜጋዋት በመያዝ ፣የታዳሽ ሀይል ምንጭ 75 በመቶ ድርሻ ይዟል፡፡ ከጂኦተርማል፣ ከንፋስና ከፀሀይ የሚገኘው ቀሪውን 25 በመቶ ድርሻ ይይዛሉ፡፡

ኢትዮጵያ ያላትን ታዳሽ የሀይል አማራጭ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የተረፈውን ደግሞ ወደ ውጭ በመላክ 50 ሚልዮን ቶን ለአየር ንብረት ዋነኛ መንስዔ የሆኑት ሙቀት አማቂ ጋዞችን መቀነስ ትችላለች፡፡

## የአረንጓዴ ልማት ስትራጂው፤ ከዕድገትና ትራንስፎሜሽን ዕቅዱ ጋር ያለው ቁርኝት

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ከአለማችን ድሃ አገራት ተርታ ብትመደብም ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድት በማስመዘብ ላይ ትገኛለች፡፡ የአለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ኢትዮጵያ በፈረንጆች አቆጣጠር 2011 ጀምሮ በቀጣይ አምስት አመታት ጠቅላላ የሀገሪቱ ምርት በአማካይ ከ8 በመቶ በላይ እንደሚያድግ ግምቱን ሰጥቷል፡፡ ካለፉት የልማት ዕቅዶች

በመነሳት የኢትዮጵያ መንግስት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዘመን ዕድገቱ በአማካይ 11 በመቶ እንሚሆን ትንበያውን አስቀምጧል፡፡ በ2002 ዓ.ም 380 የአሜሪካ ዶላር የነበረውን የሀገሪቱን የነፍስ ወከፍ ገቢ፤ በ15 ዓመታት ውስጥ 1 ሺህ የአሜሪካ ዶላር በማደረስ መካከለኛ ገቢ ያላትን አገር ለመፍጠር የኢትዮጵያ መንግስት ዕቅድ ይዟል፡፡

የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካት በ2002 ተጀምሮ በ2007 ላይ የሚጠናቀቀው የዕድገትና ትራንስፎረሜሽን ዕቅድ ስኬት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ እንደየቅደም ተከተላቸው 8 ነጥብ 6 በመቶና 20 በመቶ እንደሚያድጉ የሚጠበቁት የግብርናውና የእንዱስትሪው ዘርፍ በዕቅዱ ዘመን ማብቅያ ለሚጠበቀው ውጤት የአንበሳውን ድርሻ ይዛሉ፡፡

በዕቅዱ መሰረት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ጤፍ፣ ስንዴና ቦቆሎ የመሳሰሉት የምግብ እህሎች ከነበሩበት 19 ሚልዮን ወደ 27 ሚልዮን ቶን እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬ ከ5 ሚልዮን ወደ በአራት ዕጥፍ በማሰደግ ወደ 20 ሚልዮን ቶን በማድረስ የግብርናው ዘርፍ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

ከ ግብረናው በመቀጠል የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የተመሰረተበት የእንዱስትሪው ዘርፍ ዕድገት በዕቅዱ ዘመን መጀመሪያ ከነበረው አንጻር በዕጥፍ እንደሚያድግ ይጠበቃል፡፡ ዕድገቱ 13 በመቶ ድርሻ የነበረውን የኢንዱሰትሪ ጠቅላላ ሀገራዊ ምርት ድርሻ ወደ 19 በመቶ ያሳድገዋል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ በዕጥፍ እንድያድግ ውጥን የተያዘለት የእንዱስትሪ ዘርፍን ጨምሮ ሌሎች በአምስቱ የልማትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመናት የታቀዱ ተጨማሪ ተግባራት፤ ተጨማሪ የሀይል አቅርቦት መጠየቃቸው አይቀርም፡፡ የሀይል አቅርቦቱን ለሟሟላት አንደኛው አማራጭ የበለጸጉት አገራት በእንዱስትሪው አብዮት ወቅት ይከተሉት የነበረው፤ በአሁን ወቅት ለአለማችን የአየር ንብረት ለውጥ ዋነኛው መንስዔ የሆኑት፤ ድንጋይ ከሰል፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝና የመሳሉትን የሀይል አማራጮችን መጠቀም ነው፡፡ አማራጩ ለአየር ንብረት ለውጥን ለማባባስ ካለው አዎንታዊ አስተዋጽኦ ባሻገር፣ የሀይል ምንጮቹ ከውጭ የሚገቡ በመሆናቸው ኢትዮጵያን በመሰሉ ታዳጊ ሀገራት የሚያደርሰው የውጭ ሚኒዛሪ ጫና ከፍተኛ ነው፡፡

ሌላው አማራጭ ታዳሽ ሀይል አማራጭ ነው፡፡ አማራጩ ነዳጅና ድንጋይ ከሰልን የመሰሉ የሀይል አማራጮች ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ቀላል አይደለም፡፡ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ዕቅድን አውጥቶ መዋዕለ-ንዋይ ማፍሰስን ይጠይቃል፡፡

ኢትዮጵያ ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽኑ ዕቅድ ጎን ለጎን ያቀደችው የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ካላት ዕምቅ የታዳሽ ሀይል አማራጭ ጋር ተዳምሮ ሀገሪቱ አሁንና ወደ ፊት የሚያስፈልጋትን የሀይል አቅርቦት ችግር እንዳይገጥመው ዋስትና ሆኗል፡፡ የታላቁ የህዳሴና የግልገል ግቤ 3 የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫ ጨምሮ የአዳማና የአሾጎዳ ንፋስ ሀይል ማመንጫ በዕድገትና ትራንስፎርማሽን ዘመኑ የሚያስፈልገውን 10 ሺህ ሜጋ ዋት ለማመንጨት ከሚገነቡ የሀይል ፕሮጀክቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስኬትም ሆነ፣ ኢትዮጵያ በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር ለመፍጠር ያላትን ውጥን ላማሳካት፣ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂው የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱ እውነታዎችን ማየት በቂ ነው፡፡

## የአረንጓዴው ዕድገት አማራጭና አዋጭነት

በአለም አቀፍ ደረጃ የሙቀት አማቂ ጋዞች መቀነስ የሚችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን መፈብረክ የተለመደ ሆኗል፡፡ የቴክኖሎጂዎቹ ውጤታማነት ከሚያሳድጉት ምርታማነት ባሻገር መቀነስ በሚችሉት የሙቀት አማቂ ጋዞች መጠን ይወሰናል፡፡ በተለይም የአውሮፓ እንዱስትሪዎች እንዲለቁት የሚፈቀድላቸው የሙቀት አማቂ ጋዞች መጠን ውስን በመሆኑ ምርታቸውን ላለመቀነስ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡

የመጀመሪያው አማራጭ ሙቀት አማቂ ጋዞች መቀነስ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የቀነሱትን ጋዝ ያህል ምርት መጨመር ይችላሉ፡፡ ሌለኛው አማራጭ የአየር ንብረት ፈንድ (Climate Fund) በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ አማራጩ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ሙቀት አማቂ ጋዞችን ከሚቀንሱ አካላት በቀነሱት መጠን ክፍያ በመፈጸም ተጨማሪ ምርት ማምረት የሚያስችል አማራጭ ነው፡፡ (European trading scheme) የተሰኘው የአውሮፓ ካርበን ንግድ ድርጅት የካርበን ንግድ ስርዓቱን ያስተባብራል፡፡ እንዱስትሪዎች አገልግሎቱን ለማግኘት ለአንድ ቶን ሙቀት አማቂ ጋዞች

ለማስወገድ 15 የአሜሪካ ዶላር መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለማስወገድ በከፈሉት የጋዝ መጠን ተጨማሪ ምርት የማምረት ዕድል ያገኛሉ ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ባቀደችው የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ መሰረት የተተገበሩና በመተግበር ላይ ያሉት የአረንጓዴ ልማት ፕሮጀክቶች ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑት የአውሮፓ ንግድ ስርዓት (European trading scheme) ካስቀመጠው 15 የአሜሪካ ዶላር ባነሰ ወጪ የሚሰሩ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዕቅድ የተያዙት የአረንጓዴ ልማት አማራጮች 45 በመቶ ያህሎቹ ከተለመደው ዘላቂ ካልሆነው አማራጭ ባነሰ ዋጋ ተግባራዊ መሆን የሚችሉ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ አማራጮች የአውሮፓ ገበያ 1 ቶን ሙቀት አማቂ ጋዞች ለማሰወገድ ከሚያቀርበው 15 የአሜሪካ ዶላር ጋር ሲነጻጸር ያነሰ ቢሆንም ከተለመደው የልማት አንጻር ዋጋቸው ከፍ ያለ ነው፡፡

በአለም አቀፉ ገበያ አንጻር የኢትዮጵያ አረንጓዴ ልማት ዕድገት አማራጮች ርካሽ ዋጋ ያላቸው ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ለሚተገብራቸው የአረንጓዴ ለሚያስፈልጓት ፕሮጀክቶች የሚበቃትን ያህል ገንዘብ ከአየር ንብረት ፈንድ (Climate Fund) ለማግኘት የተሻለ ዕድል እንዲኖራት ያደርጋል፡፡

## የአረንጓዴ ዕድገት አማራጭ፤ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብና ለአከባቢው ሀገራት ያለው ፋይዳ

ኢትዮጵያ የነደፈቻቸው የአረንጓዴ ልማት አማራጮች የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ከማረጋገጥ ጎን ለጎን ለአየር ንብረት ለውጥ መንስዔ የሆኑትን የሙቀት አማቂ ጋዞችን መቀነስ ላይ ያተኮራል፡፡

ኢትዮጵያ አረንጓዴ የዕድገት አማራጭ መከተሏ እስከ 2022 ዓ.ም ድረስ ታመነጭ የነበረውን 250 ሚልዮን ቶን ሙቀት አማቂ ጋዞች ወደ ህዋው እንዳይቀላቀል ትከላከላለች፡፡ ይህ ደግሞ በተጠቀሰው ጊዜ ከተለመደው ዕድገት አማራጭ አንጻር የሚመነጨውን ሙቀት አማቂ ጋዞች 64 በመቶ መቀነስ ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በተለመደው የዕድገት አማራጭ 1 ነጥብ 8 ቶን ይደርስ የነበረውን የነፍስ ወከፍ

የማመንጨት መጠን የአረንጓዴ የዕድገት አማራጭን በመጠቀም ወደ 1 ነጥብ 1 ቶን ማድረስ ይቻላል፡፡

የአረንጓዴ ልማት የዕድገት አማራጭ አለም አቀፉን ሙቀት አማቂ ጋዞች ከማስወገድ በተጨማሪ ለአከባቢው ሀገራት ትርፍ የኤሌክትሪክ ሀይልን በርካሽ ዋጋ ማቅረብ አስችሏታል፡፡ ርካሽ የሀይል አቅርቦቱ አከባቢያዊ ሀገራትን በኢኮኖሚ ከማስተሳሰር ጎን ለጎን ከተለማደው ካርበንን መሰረት ካደረገ የሀይል አመራረት እንዲወጡ በማድረግ ለአለም አቀፉ አረንጓዴ ልማት ዕድገት ተጨማሪ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ኢትዮጵያ ለሱዳንና ጅቡቲ እንደየ ቅደም ተከተላቸው 100 እና 50 ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ሀይልን መላክ ጀምራለች፡፡ ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ ብድር ወደ ኬንያ ለመላክ የኤሌክትሪክ ሀይል ተሸካሚ መስመር እየተዘረጋ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ ወደ ኡጋንዳና የመን የኤሌክትሪክ ሀይልን ለመላክ የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል፡፡

ኢትዮጵያ በመጪዎቹ ከ10 እስከ 15 ዓመታት 5 ሺህ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሀይልን ወደ ውጭ ለመላክ ማቀዷን የውሃ፣መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ገልጿል፡፡ ግብጽን ጨምሮ ለ13 ሀገራት በመላክ 1 ቢልዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት አቅዳለች፡፡

## የአረንጓዴ ልማትተግዳሮትና መፍትሄው

የአረንጓዴ ልማት ፕሮጀክቶችን ለማከናወን የሚያስፈልገው የመነሻ መዋዕለ-ንዋይ መጠን በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ለፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም ተግዳሮት መሆኑ አልቀረም፡፡ ኢትዮጵያ በቀጣይ 20 አመታት ለሀይል ማመንጫ መሰረተ ልማቶችን ብቻ ለመገንባት 38 ቢልዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚያስፈልጋት የአለም ባንክ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2011 ይፋ ያደረገው ሪፖርት ያመለክታል፡፡ ከአረንጓዴ ልማት ባሻገር ሌሎች በርካታ መሰረተ ልማት ግንባታ ለሚጠብቃት ኢትዮጵያ፣ የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን መሸፈን ከባድ ይሆናል፡፡

በዕድገትና ትራንፎርሜሽን ዕቅዱ ሀገሪቱ የሚያስፈልጋትን የመሰረተ ልማት ግንባታ ወጪ ለመሸፈን ያስችላት ዘንድ ዝቅተኛ የነበረውን የቁጠባ መጠን ከዕጥፍ በላይ ለማሳደግ ውጥን ተይዟል፡፡ በአምስቱ ዕቅድ አመታት ከ11 ነጥብ 9 ወደ 27 ነጥብ 5 በመቶ እንደሚያድግ

የሚጠበቀው የሀገሪቱ የቁጠባ መጠንም ከመደበኛ መሰረተ ልማት ግንባታ በተጨማሪ የሚያስፈልገውን የአረንጓዴ ልማት መዋዕለ-ንዋይ ለመሸፈን በቂ አይደለም፡፡

የሚያስፈልገው ወጪ ከ55 በመቶ በላይ የሚሆነው በውጭ ሚኒዛሪ መልክ የሚያስፈልግ መሆኑ በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ ጫና ማሳደሩ አይቀርም፡፡

ለአረንጓዴ ልማት የሚያስፈልገውን የገንዘብ ጉድለት ለመሸፈን የታቀደው አለም አቀፉ ማህበረሰብ የአየር ንብረት ፋይናስ ስርዓት ነው፡፡ የገንዘብ ምንጩ በሌሎች ታዳጊ ሀገራትም የሚፈለግ መሆኑ ገንዘቡን ለማግኘት ፉክክሩ ከፍተኛ መሆኑ ነው የሚነገረው፡፡ በዚህ ምክንያት የካፒታል ዕጥረቱ ሀገሪቱ ለቀየሰችው የዘላቂ ኢኮኖሚ አማራጭ ደንቃራ ሊሆን ይችላል፡፡ ነዳጅ የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች በሚጓዙበት መንገድ ፋንታ ለኤሌክትሪክ ባቡር የሚያስፈልገውን መሰረተ ልማት ለመገንባት የሚያስፈልገው መዋለ-ንዋይ በጣም ከፍታኛ ነው፡፡ ነገር ግን ከተጠናቀቁ በኃላ አዋጭና ዘላቂ አማራጭ ነው፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ያለ ታዳጊ ሀገር ኢኮኖሚው ዘላቂ እንዳይሆን ከሚያደርግ አማራጭ በመቆጠብ፤ አስቸጋሪ አማራጭ ቢሆንም የዘላቂ ኢኮኖሚ አማራጭ መጠቀም ቀጣይ ትውልድን ታሳቢ ያደረገ የአርቆ አሳቢዎች አማራጭ ነው፡፡

## እንደ ማጠቃለያ

በመጨረሻም ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ተጽዕኖ መቋቋም የሚያስችል የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ አገሪቱን ወደ ዘላቂ የአኮኖሚ ዕድገት የሚመራ አማራጭ ቢሆንም የአለም አቀፍ ማህበረሰብ ድጋፍ የሚያስፈልገው ነው፡፡

አገሪቱ የአረንጓዴ ልማት ስራቴጂወን ለመተግበር የሚያጋጥማትን ችግር እየተጋፈጠች በፈረንቹ አቆጣጠር እስከ 2017 መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር ለመሆን የያዘችውን ውጥን ለማሳካት ሀገራዊ ንቅናቄና ትብብርን የሚጠይቅ ነው፡፡